ሰኔ 6ቀን 2010ዓም

# <u>የደስታ መግለጫ</u>

ለተከበርከው የአማራ ሕዝብ፣ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ(አብን) አመራርና አባላት እንዲሁም ደጋፊዎች በያላችሁበት!

እንኳን ለአማራው ሕዝብ አለኝታ ድርጅት <u>**ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ**</u> ምሥረታ አበቃን።እንኳን ደስ ያለን እላለሁ።

በክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ መሪነት ተቋቁሞ ከነበረው መዐሕድ ወዲህ <u>ኢትዮጵያ ውስጥ የአማራ ድርጅት የመመሥረትን አሥፈላጊነት</u> በተደጋጋሚ ሥፅፍ ኖሬ፣ ዛሬ ተግባራዊነቱ ዕውን ሲሆን፣ ህልም እንጅ ዕውነት መሆኑን ለማመን አዕምሮዬ ዘግይቶ በመቀበሉ፣እጄን አሥቀድሜ አሁንም ዘግየት ብዬ ይችን ፅሁፍ ለመፃፍ ተገደድኩኝ።

***ወገኖች ሆይ!***

እንደሚታወቀው ዛሬ አማራው ከሚገኝበት አሥከፊ ሁኔታ ከተነሳን <u>"እንኳን ለኢትዮጵያ አንድነትና ለአገር ሉዐላዊነት ሊቆም ቀርቶ፣የሚፈፀምበትን የማያባራ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለመመከትና ለራሱ ህልውና መቆም አዳግቶት፣በመኖርና ባለመኖር መካከል የሚገኝ ሕዝብ</u> ከሆነ አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል።

ከእንግዲህ ወዲህ የአማራው ሕዝብ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሠጥቶ መታገል ያለበት<u> ራሱን ከመጥፋት ለማዳን መሠረታዊና ወሳኝ ጥያቄ የአማራው ህልውና</u> እንደሆነ ተገንዝባችሁ፣ለተግባራዊነቱ የአማራን ዘር በአንድነት ሰባስቦ ሊያታግልና ሊታገል የሚችል በራሱ ወገኖች አገር ውስጥ በተቋቋመ ጠንካራ የአማራ ድርጅት ተመርቶ ግቡን ሲመታ እንደሆነ ተረድታችሁ፣ <u>**የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄን(አብን)**</u> በማቋቋማችሁ ምሥጋናዬ የላቀ ነው። በቃላት ልገልፀው ከምችለው በላይ ልባዊ ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ። አኮራችሁን።

<u>**ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ድርጅት የመመሥረቱ ጥቅም ከብዙ በጥቂቱ!**</u>

(1ኛ)በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖረውን የአማራ ዘር በአንድ ሰባስቦ በአንድ አመራር ሥር እንዲታገልና የአማራው ሕዝብ ህልውናውን ብሎም መብቱን እንዲያስከብር ንቃት ያጎናፅፈዋል፣

(2ኛ)ከእንግዲህ አማራው ራሱ በህይወቱ እየከፈለ የሚያገኛቸውን ድሎች፣እንደከዚህ ቀደሙ አማራው እየደማ በጓዳ በር ብቅ ለሚሉና ለሚያደቡ የሀሰት አንድነቶችና የሥልጣን ጥመኞች አሣልፎ ሲሰጥ እንደኖረው ሳይሆን፣በራሱ በአማራው ፍላጎት በተቋቋመው <u>በአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ</u> ድርጅት እያሥመዘገበ ለራሱ መጠናከሪያነት እንዲጠቀምበት ይረዳዋል፣

(3ኛ) በ1983ዓም እንደተደረገው ሁሉም ነገዶች የየጎሳዎቻቸውን ተወካዮች ለሽግግር መንግሥት ሲያዘጋጁ፣ አማራው ያለተወካይ ቀርቶ እንደተጠቃው "ሞኝን እባብ ሁለት ጊዜ ነደፈው" እንዳይሆን ይረዳዋል፣

(4ኛ) አማራው ለህልውናው ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራቱ የግድ ነው።ነገር ግን ለወደፊት ህልውናው እየተረጋገጠ ሲመጣ፣ከሌሎች ጎሳዎችም ጋር ለመዎያየትም፣ለመቀራረብም ሆነ አብሮ ለመሥራት፣ ብሎም የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር(ትነግ) ከገባበት ወቅት አንስቶ በተግባር የጠፋውንና በአፍ የሚደጋግመውን የኢትዮጵያ አንድነትም ለማምጣት፣ <u>**ከእንግዲህ አማራን በሚወክለው የአማራ ድርጅት አማካይነት እንጅ በሞግዚት አይሆንም**</u> ማለት ነው።

(5ኛ)እሥከዛሬ ቀደም ብለው በተቋቋሙ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ጠላት በአባልነት ወይም በደጋፊነት ሠርጎ በመግባት ድርጅቶችን ሲበታትን ተመልክተናል።ሥለዚህ አፍራሽ የሆኑ ኃይሎች እናንተን መሥለው በመካከል በመግባት ከአማራ በላይ አማራ ሆነው በአሉባልታም ሆነ በተለያዩ መንገዶች **<u>የአብን</u>**ን ጤንነት እንዳይፈታተኑት፣ በየጊዜው ሁኔታዎችን በዜናና በጥናት መልክ እየገመገሙ፣እርስ በእርስ በቀላሉ በመናበብና ራስን ይበልጥ የማንቃት ጥብቅ አሠራር እንዲኖርና እንዲለመድ ያደርጋል።

**ማሳሰቢያ**! በ1983ዓም ከአማራው በሥተቀር ሁሉም በየጎሳዎቻቸው ተሰባስበው፣የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ጥለው፣የዘርና የቋንቋ ዘጠኝ(9)መንግሥታትና ባንዲራዎች መሠረት ያደረገ የፀረ አማራና የፀረ ኦርቶዶክስ ህገ መንግሥት ሲያፀድቁ፣<u>የኢትዮጵያ አንድነት ከህገ መንግሥቱ</u> ተፍቋል።ይህ ህገ መንግሥት ዛሬም ድረስ አለ።

አማራው! ይህንን <u>ተጨባጩን ሁኔታና ዕውነታ</u> ማየት ተስኖት ሥለሚመኘውና ሥለፈለገው ብቻ የኢትዮጵያን አንድነት የሙጥኝ ብሎ <u>የህልውናው ዋሥትና የሆነውን በአማራነት መደራጀትን</u> ከልብ ባለማመኑ፣በአማራ ጠሎች ሀያ ሰባት (27)ዓመት ተዘመተበት።ዛሬ ግን ይህንን ተጨባጭ ዕውነታ ተረድቶ መጀመሪያ ለአማራው ብቸኛ አማራጭ የሆነውን የአማራን አንድነት አጠናክሮና ታግሎ ማንነቱንና ህልውናውን ማለትም የመኖር ዋሥትናውን ለማረጋገጥ ቅድሚያ ሰጥቷል።ይህ እሰዬው ያሰኛል።

ይህ ዛሬ ያለው <u>"ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ህገ መንግሥት እሥካልተለወጠ ድረስ</u>"፣አንድ ቦታ እሳቱ ቢበርድ፣ሌላ ቦታ እየተቀጣጠለና ሁኔታው እያገረሸ "የኔ ፣የአንተ" በሚሉ የዘርና የክልል አባዜዎች በመወጠር መገዳደሉንና መፈናቀሉን ለማስቆም ዶክተር አቢይ <u>ጊዜያዊ እንጅ</u> <u>ዘላቂ መፍትሄ</u> አይኖረውም።

ዛሬ ዶክተር አቢይ የሚለው ኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት ከቃል አያልፍም።ሆኖም ግን ይህ በእነዶክተር አቢይ የተጀመረው ጥገናዊ ለውጥ ለአማራው የመደራጀት በር ሥለከፈተ፣<u>አብን</u> የተገኘውን ቀዳዳ በመጠቀም ይትጋ እላለሁ። የአማራው ሕዝብ በራሱ ድርጅት አማካይነት ትግሉን አጠናክሮና ጎልብቶ ሲወጣ <u>ወደሥር ነቀል ለውጥ</u> ሊሸጋገር እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።እዚህ ላይ ግንዛቤ ውስጥ ማሥገባት ያለብን "ይህች ዓለም የምታጅበው ጉልበት ያለውን ብቻ እንደሆነ አውቀን፣ አማራው ህልውናውን ሊያስከብር የሚችለው በራሱ ጥረት ብቻ እንደሆነ ማመን ይገባዋል።ከዚህ ውጭ ሌሎች የእኛን ችግር እንደማይፈቱልን እንወቅ።

ሁላችንም እንደምንገነዘበው በአንድ ወቅት በእነክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ተቋቁሞ፣ቁጥራቸው የማይናቅ አማራዎችን ህይወት የታደገውን "መዐሕድን" <u>በንቃተ ህሊና ጉድለት ምክንያት</u> ከመሪው ጋር ካሥበላነበት ጊዜ ጀምሮ፣ ለብዙ ዓመታት አማራው ያላንዳች "ብሶት ነጋሪ" ሲቀጠቀጥ ከኖረ በኋላ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በውጭ አገር ድርጅቶች ብቅ ብለው የአማራውን ሠቆቃ ማጋለጥ ተያያዙት።ይህ በዚህ እንዳለ በአገር ቤት ብሶት የወለደው የሐምሌን 5ቀን 2008ዓም ትግል የለኮሰውና ያቀጣጠለው አብዛኛው ወጣት፣ ትግሬዎች ሲገቡ ከ10ዓመት በታች የነበረና ከገቡ በኋላ የተወለደ ነው ማለት ይቻላል።

ይህም **<u>በአብን</u>** ዙሪያ የተሰበሰበው ትንታግ ወጣት ትውልድ! "አማራው በአማራነት ብቻ እራሱን እያጎለበተ በሄደ ቁጥር፣ የሰቆቃውን ጊዜ ያሣጥራል" ብሎ እንደተነሳ ይሰማኛል።

**<u>በአገርና በውጭ የምንገኝ አማራዎች! ወጣቱ ለማንነቱ ሲዋደቅ በተግባር ከጎኑ ለመቆም ያለን የሥራ ድርሻ ምንድነው?</u>**

(1ኛ) የቆየነውና አንጋፋዎቹ በተለያዩ ጊዜያት ትግል በየፈርጁ በማካሄድ ብዙ ሙከራዎች ብናደርግም ፈተናውን ያላለፍንና የወደቅን ሥለሆነ ቆም ብለን ራሳችንን በመመርመር፣ትግሉን አቀጣጥሎ በባለቤትነት ይዞ መሥዋዕትነት እየከፈለ የሚታገለው የአማራ ወጣት! የሚያካሄደውን

ትግል እየመራ ግብ እንዲያደርሰው ከጎኑ በመቆም ማበረታታትና አሥፈላጊውን ምክርና ዕርዳታ ማቅረብ ከእኛ የሚጠበቅ ነው።

ወጣቱ! "ምክር ለጋሽ እፈልጋለሁ" ካለ ምክር መሥጠት።ወጣቶቹ!ለትግላችን ይጠቅማል የሚሉትን ይቀበሉታል፣ካልጠቀማቸው ይጥሉታል።

ነገር ግን "ራስን ማወቅ ትልቅ ዐዋቂነት" እንደሆነ መገንዘብ ተሥኖን፣**የአብን** ወጣቶች "ምሩን ሳይሉ እንመራችኋለን፣ወክሉን ሳይሉ እንወክላችኋለን፣ በተለያዩም መንገዶች ጣልቃ በመግባት ተፀዕኖ እንፈጥራለን፣ካልሆነም እርዳታ ላለመሥጠት አሻጥር እንሠራለን" ካልንና በውጩ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው የእርስ በእርስ መኳሸምና የመጠፋፋት አባዜ ጣራ ከነካ፣እሥከዛሬ የሚደግፈን ሕዝብ ማንነታችንን በሚገባ ሲገነዘብ ድጋፉን ያነሳል።ድርጅቶቹም ያለጥርጥር ከጊዜ ጋር ወዳቂዎች ይሆናሉ።ግለሰቦችም እንዲሁ።

ይህ ደግሞ በኢሕአፓና በመኢሶን ቀጥሎም በቅንጅት ታይቷል።በዚህ መካከል የሚጎዳው ግን በትግሬ ጦር እንዲጠፋ የታወጀበት ወገናችን እንደሆነ መገንዘብና ከችግር ፈጣሪነት መቆጠብ ያሥፈልጋል።

(2ኛ) እንደሚታወቀው በክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ መሪነት ተቋቁሞ የነበረው **መዐሕድ** እዚያው ሕዝቡ መካከል ተመሥርቶ ሲታገል፣ በውጭ ሀገራት የምንኖረው የአማራ ተወላጆች በራሳችን አነሳሽነት፣በየምንኖርባቸው ሀገራት የአማራን ሥም የያዙ የተለያዩ መጠሪያዎች ያላቸው የድጋፍ ድርጅቶች አቋቁመን፣ በወዶ ገባነት በመዐሕድ አመራር ሥር ተሰልፈን፣ገንዘብ እየሰባሰብን ለመዐሕድ በመላክና በማጠናከር፣ትብብራችንን ሙሉ በሙሉ እናሳይ ነበር። ለምሳሌ እኔ በምኖርበት አገር በእኔ ሊቀመንበርነት ይመራ የነበረው የድጋፍ ድርጅት መጀመሪያ ላይ ይህንን ሲያደርግ ቢቆይም፣ ወደኋላ ላይ ግን በተለያዩ ሀገራት የምንገኘው የድጋፍ ድርጅቶች በአንድ ቦርድ ተሰባስበን በአንድ መንገድ ለመላክ በቅተን ነበር።

ዛሬም በውጭ ሀገራት በሚገኙ በአማራ ሥብስቦች የተመሠረተው **አድማስ** ፣ **ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄም** መቋቋም ደስታውን ገልጿል። ይህ እሰዬው የሚያሰኝ ተግባር ነው።የ**አድማስ** መፈጠር ከጥቅሞቹ አንዱ ለትግላችን መቀራረብን ከመፍጠሩም ባሻገር በሁላችንም ሥም ገንዘብ አሰባስቦ በመላክ በውጭ አገር ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ጠንካራ"የድጋፍ ድርጅት እንዲሆን እንሥራ።ለዚህ ተግባር ብቁ ሆኖ ለመገኘት ዓለም አቀፋዊ አሰባሰብን ከግምት ውስጥ አሥገብቶ፣አመራሩን ግልፅ አድርጎ መመሪያ አውጥቶ እንቅስቃሴ ቢጀምር ሁላችንም ከጎኑ በመሆን እናጠናክረዋለን የሚል ዕምነት አለኝ።

ውጭ አገር የምንገኝ በግልም፣በቡድንም ሆነ በስብስብ የምንገኝ አማራዎች! የግል ፍላጎት፣የድርጅት ፍቅር፣እኔ ያልኩት ካልሆነ እና የሥልጣን አባዜ ካልተጠናዎተን በሥተቀር ሁላችንም በዚህ በያለንበት አገር ሆነን ኢትዮጵያ የሚገኘውን የአማራ ሕዝብ በሪሞት ኮንትሮል እንመራዋለን ብለን እንደማናስብ እገነዘባለሁ።

ሥለሆነም ቀደም ሲል እኛ ለእነፕሮፌሰር አሥራት መዐሕድ፣ የድጋፍ ድርጅቶች ሆነን እንዳገለገልነው ሁሉ፣ ዛሬም በአድማስ ዙሪያ የተሰባሰብነውም ሆነ የምንሰባሰበው አማራዎች ፣አድማስን አጎልብተን የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ የድጋፍ ድርጅት በማድረግ ገንዘብ ለማሰባሰብ እሥከምንበቃ ድረስ ፣የአማራው መፈናቀልም ሆነ የችግሩ ሥፋት ፋታ ሥለማይሰጥ፣እያንዳንዱ የአማራ ድርጅት የቻለውን ያህል ገንዘብ ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ(አብን) በመላክ አብን ተንቀሳቅሶ አማራውን ሊደርስና ሊያደራጅ እንዲችል ብናደርግ ይመረጣል።

በተለይ በውጭ አገር **አድማስ** እሥከሚጠናከር ቀደም ብሎ ተቋቁሞ ያገኘሁትና ዕርዳታውን ለአማራው ሕዝብ ያደርሳል በሚል እሳቤ ላቅ ያለ የማይናቅ ገንዘብ የከፈልኩት **ለሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት** በመሆኑና ያገባኛል መብቴም ነው ብዬ ሥለማስብ ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ ዕርዳታ በማድረግ እንዲተባበር ሥጠይቅና ጥሪዬን ሳስተላልፍ ከታላቅ ትህትና ጋር ነው።

በመጨረሻ ***በማሃታማ ጋንዲ*** ጥቅስ ልሠናበታችሁ “አዲስ ሀሳብ ሥታፈልቅ መጀመሪያ ይዘጉሀል፣ቀጥሎ ይሥቁብሀል፣ከዚያም ይታገሉሀል፣በመጨረሻ ታሸንፋለህ።”

አያሌው ፈንቴ